# ሕብረት ሀቅና ግልጽነትን ይጠይቃል

## ከፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ሬዲዮ ወቅታዊ ሐተታ

የኢትዮጵያ ሕዝብ ተባበሩ ወይም ተሰባበሩ ያለበት ጊዜ ባይኖርም ህብረት ቢደረግ ክንዳችን ይጠነክራል ብሎ ለማመኑ ግን ምስክር መጥራት አይኖርብንም። ሕብረት የሕዝብን ክንድ ያፈረጥማል፤ ጠላትን ያዳክማል። በነጻ ጋዜጠኛ ሽፋን ዋና ወያኔያው ተልኮአቸው ያን ትውልድና ኢሕአፓን መውቀጥ የሆነው እንደሚለፍፉት ሕብረትን በተመለከተ ኢሕአፓ ከዛሬ 40 አመት በፊት የነበረውን አቅዋም በተመለከተ ያያኔ ዴሞክራሲያ ግልጽ አድርጎ የጻፈውን ማቅረብ አስፈላጊ ነው። እንጥቀስ--

ከ ዴሞክራሲያ በ 16/12/1966 እትም ገጽ 6 የሚከተለውን በሰፊው እናቀርባለን፡

*"የለውጡ ዓላማ የጥቂቶችን በዝባዥነት የሚፈቅደውን ጨቋኝ መንግስት አፍርሶ፡*

*ሀ/ መሰረተ ሰፊና ተራማጅ ዴሞክራሲያዊ የሆነ የፖለቲካ ስራዓት መመስረትና፤ ዴሞክራሲያዊ ፑብሊክ ማቋቋም፤*

*ለ/ "መሬት ለአራሹ" የሚለውን የሕዝብ ጥያቄ ስራ ላይ ማዋል፤*

*ሐ/ ከባዕድ ሀገሮች ተጽዕኖና ብዝበዛ ነጻ የሆነ ብሔራዊ ኤኮኖሚ በመንገባት የሕዝቡን የኑሮ ደረጃ ማሻሻል፤*

*መ/ የብሔሮች እኩልነት ሙሉ በሙሉ ታውቆ ፈቅዶ በመዋሀድ በተባለው መርሀ መሰረት የሚፈልጉትን የመንግስት ዓይነትና ስርዓት በእኩልነት፤ በወንድማማችነትና በህብረት እንዲያቋቁም ማድረግ፤*

*ሠ/ በወንዶችና በሴቶች መካከል የእኩልነት መብት ማስከበርና የሴቶችን መብት መጠበቅ፤*

*ረ/ ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ የትምህርት ስርዓትና ባሕል በመገንባት፣ ትምህርት በነጻ ለሁሉም እንዲዳረስ ማድረግ፣ ለሕዝቡ የጤና አጠባበቅ አገልግሎት ማዳረስ፣*

*ሰ/ የጦር ሀይሉ ለፈላጭ ቆራጭ ነጋሲና ግብረአበሮቹ ወይንም ለአንድ ወታደራዊ አምባገነን ሳይሆን ሕዝቡንና አገሪቱን  የሚያገለግል እንዲሆን  አስፈላጊ የሆኑትን እርምጃዎች መውሰድ፣*

*ሸ/ በገለልተኛነትና በሰላም ላይ የተመሰረተ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ መከተል፣...የኢትዮጵያን ብሔራዊ ነጻነት የሚቀንሱ፣ የበላይ ገዥነትን የሚቃረኑ፣ በእኩልነት ላይ ያልተመሰረቱ ውሎችን ማፍረስ መሆን አለበት።*

*ይህንን ስራ ላይ ለማዋል የሕዝብ ወገን ሁሉ ለማጠቃለል የሚችል ሰፊ ግንባር መቋቋም አለበት። <u>ይህን ስንል ባሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ አንድ ፓርቲ ብቻ ይኑር ማለታችን አይደለም።</u> ፓርቲ የአንድ መደብን ጥቅም የሚያስጠብቅ የፖለቲካ ድርጅት ነው። ብዙ መደቦች እስካሉ ድረስ ብዙ ፓርቲዎች ይኖራሉ። ግንባር ደግሞ ጊዜያዊ ቢሆንም ተመሳሳይ ጥቅም ያላቸውን ብዙ መደቦችን በተወሰነ ፕሮግራም መሰረት፣ በአንድነት የሚሰበስብ የፖለቲካ ድርጅት ነው። አንድ የፖለቲካ ግንባር የሚቋቋመው ከልዩ ልዩ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ከሕዝባዊያን ድርጅቶች፣ ዴሞክራሲያውያን ጥያቄዎችን /ለምሳሌ እኩልነት፣ ነጻነት/ ይዘው ከሚነሱ የሀይማኖትና የብሔር መሪዎች፣ አገር ወዳድ ከሆኑ ግለሰቦችና ከመሳሰሉት ነው። እነዚህ ክፍሎች ሁሉ አብረው የሚሰለፉት ሁሉም ዴሞክራሲያዊ መብቶቻቸውን ስለተነፈጉ፣ ሁሉም በመሳፍንቱ በከፍተኛ ከበርቴዎች ስለተጨቆኑ ነው። አንድ አይነት ጠላት አላቸው። አንድ አይነት ጊዜያዊ ጥቅም አላቸው። ለሁላቸውም ይህን ጊዜያዊ ፕሮግራም / መርሃ ግብር/ ማሟላት ይበልጥ ወደፊት ለማራመድ ለማሻሻል መንገድ ይከፍትላቸዋል። ጊዜው የሚጠይቀው፣ እውነተኛ ለውጥ ሊመጣ የሚችለው በዚህ ዓይነት ዘዴ እንጂ ከሕዝብም ተነጥለው ላይ ላዩን ብቻ የተመለከተ በደርጉ ውስጥና አካባቢ በሚዶልቱት ሰዎች አማካይነት ለውጥ ሊመጣ ፈጽሞ አይችልም ።”*

በ1966 ኢሕአፓ ያለው ዛሬም ህቅ ሆኖ ሲገኝ መቼም ቢሆን መቼም ድርጅቱ እኔ ብቻ፣ እኔ ያልኩት ካልሆነ ሲል ተደምጦም አያውቅም። ህብረትን ከሕዝብ ጥቅምና ጥያቄ አንጻር

መያዝ ተገቢ መሆኑን፤ የጋራ ጥረትንና ለውሱን ወቅትም ቢሆን የጋራ ወይም ተመሳሳይ አቅዋም መያዝ አስፈላጊ መሆኑን በ2005 ሳይሆን በ1966 ያስገነዘበውና በዚህም መልክ ሰፊውን ሕዝብ ሊያሰባስብ የጣረውና የታገለው ኢሕአፓ ነው። ደርግም ለይስሙላ ግንባር ሲል ኢሕአፓ የሰጠው መልስ ከላይ ከተጠቀሰው ጋር ተመሳሳይ ነው። ሀቁ ይህ ነው። ለማንኛውም ድርጅቱ ግንባር በሚል መጻፍ መናገር ብቻ ሳይሆን በገቢርም ትግሉን ለጠቀሙ የግንባር ጥረቶች ሁሉ የአቅሙን አስተዋጾዖ ማድረጉን ሁሉም ያውቃል። ዛሬም ለህብረት ጥረቶች መደረጋቸው ተገቢ በመሆኑ ኢሕአፓ በየጊዜው በመሰለው መንገድ ጥሪውን አስተላልፏል። የሕዝብ ጎራ የተባለው ያለውን ድክመት -- ያውም ወያኔ የሚያውቀውን--በመጥቀስ እርምት ሲጠቁምም ቆይቷል። ይህን አቅዋምና ጥረቱን ለማደናቀፍ ደግሞ የወያኔ ቅጥረኞችና የፖለቲካ ተምቾች አሁንም እየዘመቱበት ነው። ነጋ ጠባ ሞተልን ደከመልን እያሉም በራሳቸው ቅዠት ይናውዛሉ በከንቱ። ወደ ዋናው ርዕስ ስንመለስ ደግሞ ሕብረት ለመመስረት ማነው ጠላት፤ ለምን ግብ፡ እንዴት ትግል በሚሉት ጥያቄዎች ላይ ተመሳሳይ አቅዋም አመለካከት ሊኖር ይገባል። ሕብረቱም በገለባ ቡድኖች ሳይሆን ሚዛን ባላቸውና ፖለቲካዊ ህልውና ባላቸው ድርጅቶች መሀል መሆን አለበት። ሕብረቱ በተግባራዊ ትግል ማለትም በትግሉ መስክ በመገኘትና በመታገል ዙሪያ መሆንም አለበት ተብሏል። ይህን መንገድ አሌ ብለው የሚገኙ ክፍሎች ደግሞ የራሳቸውን መንገድና ዘዴ፤ አቅዋም ማቅረብና ሕዝብን ማሳመን ይጠብቅባቸዋል።

ግልጽነት ግን ወሳኝ ቀዳሚ መሆን አለበት። ኣቅዋምን በተመለከተ። የወያኔ ቅጥረኛ ሆኖ፤ ጸረ ትግል ሆኖ፤ በታኝ አንጃ ሆኖ ማንም አልነቃብንም በሚል በህዝብ ጎራ ገብተው ለማተራመስ የሚፍጨረጨሩት ሁሉ መራገፍ ያለባቸው ናቸው። ጽዳት ወሳኝ ነው። ትግልም ላይ የሚጣበቁ ትኋኖች ጨጎጊቶች አሉና ወደፊት ለመጓዝና ክፉ ጠላትን ለመጋተር በቅድሚያ ተባዮቹን ማስወገድ አስፈላጊ ነው። እነ ክህደቱና መሰሎቻቸው ያደረሱትን ጉዳት ልንረሳ አንችልም። ዛሬም የህብረት ጥረት እንዳይሳካ የሚጥረው ወያኔ ብቻ ሳይሆን ከሕዝብና ከታጋይ ተመሳስለው በገቢር ለወያኔ ያደሩትና የሽፉን ጭምብሎቹን ያጠለቁትም ናቸው። በዴሞክራሲያ ከ 40 አመት በፊትና ጀምሮ የተገለጠው ሀቅ የታሪክን ሂደት ሆነ የትግልን ውጤት በተንኮልና በሸር ለመለውጥ ሆነ ለመቆጣጠር የማይቻል መሆኑን ነው። የሕዝብ ተሳትፎና የህዝብ ፍላጎት ነው መሰረቱ ለለውጥ። ሌላ መንገድ የለውም። ጨቋኞች ሆኑ አምባገነኖች ውሎ አድሮ ይንኮታኮታሉ--ለመቼ መልሱ በሕዝብ ትግል የሚወሰን ነው እንጂ ውድቀታቸው አይቀሬ ናት። በሕዝብ ደም የነገዱም፤

የታጋዮችን ህብረት ያደናቀፉም ሁሉ ቀን ጠብቆ ሕዝብ ይፋረዳቸዋል። እስከዚያው ግን የሀገርና የሕዝብን ጥቅም በማስቀደም የሚሰባሰበውን ሁሉ ይዞ መታገል ያስፈልጋል። ኢሕአፓ ይህን በተግባር አውሎ ደም ከተቃባቸው ጋር ሳይቀር ለሀገር ጥቅም ሲል ሕብረት መስርቷልና አሁንም ቢሆን ቅድሚያ የሚሰጠው ህልው ሊሆን የሚችል፣ በትግል የሚሰማራና ውጤት ሊያስገኝ በሚችል ህብረት መሳተፍ ነው። በኢትዮጵያ አንድነት ጥላ ስር ለኢትዮጵያ ከሚታገሉ ህልው ድርጅቶች ጋር መታገል ነው የኢሕአፓ አቅዋም። በዚህ በኩልም አሁንም ጥረቱን ይቀጥላል -- ትግሉን ሳያቋርጥ።

በፖለቲካው መድረክ የወያኔ ቅጥረኞች በሰፊው ተሰማርተዋል። ወያኔ ቀውሱ ሲበዛ አፍራሽ ጥረቱን ይበልጥ ያባብሳል። በየድርጅቱ ያሉ ሰርጎገቦቹን ተጠቅሞ ድርጅቶችን ለማፍረስ ይራወጣል። የባዕድ ቅጥረኞችም የሆኑት ወያኔ ጠላት የሚላቸውን ድርጅቶች ለማፍረስ ለመበተን ይንቀሳቀሳሉ። ይህንንም ጠንቅቆ ማወቅ ተገቢ ነው። ድርጅቶችም እርስ በርስ ሊያጣሏቸው የሚጥሩትን ነቅተውባቸው አላማቸውን ማክሸፍ አለባቸው። ይህ አስፈላጊ እርምጃ ነው። ድርጅቶችም ራሳቸውን ከጥቃት መከላከል ይገባቸዋል -- ለወያኔና ቡችሎቹ ጥቃት ሰለባ መሆን የለባቸውምና። ይህ ጠቃሚ ጥቆማ ነው ብለን እናምናለን። ጸረ ወያኔ ትግላችንን ለማስተባበር ሙሉ ጥረት እናድርግ።

ነሐሴ 2005 ዓ. ም.